# <u>የዓለም ኑሯችን!</u>

መኖር ስንጀምር ዓለሚቱ ላይ
የላዩ ታች ወርዶ የታቹ ከላይ
ሳይቻል የሚቻል !
ሲቻል የማይቻል !
የዚህ ዓለም ኑሮ ፤
ጣፋጭ መስሎ መሮ !
ላንችል ችለን
ልንችል ቆርጠን
ደፋ-ቀና ብለን
ዳገቱን ወጥተን
ቁልቁለት ወርደን
አንዳንዴም ሲከፋን
አልፎም ሲያስቀን
አሸነፍነው ስንል እያሸነፈን
ሁሉም በጊዜ ውስጥ
ሲመር ሲጣፍጥ !
ላንችል ችለን
ልንችል ቆርጠን
ተሸከምነው እንጂ አልተሸከመን !!

በዓለም ላይ ሆነን
ዓለም ተጭናን
መላዋ ጠፍቶብን
ስታባዝነን
ከበርንባት ስንል ስታደኸየን
ጠገብንባት ስንል እያስራበችን
ተሾምንባት ስንል ሹምሽር አልብሳን
ጤንነት ስንሻ
በሕማም ገርፋን
ነፃ ነን እያልንም ባርነት ለብሰን
በዲሞክራሲ ስም ዲክታተር ገዝቶን
መተንፈስ አቅቶን ፍጹም ታፍነን
ዲክታተሮችና የዓለም በዝባዥ ኃይላት
ሆነው እጅና ጓንት
በገዛ ሀገራችን እንዳይኖረን ኩራት
በስደት አባዝነው ግራ በማጋባት
ይኸን ሁሉ መከራ
የማንገፋው ጋራ
ለመቻል ብለን
እያቃሰተን
ላንችል ችለን
ልንችል ቆርጠን
ደፋ ቀና ብለን
ዳገቱን ወጥተን
ቁልቁለት ወርደን
አንዳንዴም ሲከፋን
አልፎም ሲያስቀን
አሸነፍነው ስንል እያሸነፈን
ሁሉም በጊዜ ውስጥ
ሲመር ሲጣፍጥ
ላንችል ችለን
ልንችል ቆርጠን
ተሸከምነው እንጂ አልተሸከመን !!